# በአማራነት ዙሪያ እየተነሳ ያለው አሉባልታና የዘር አደረጃጀት ለድርጅታችን ህልውና በጣም አደገኛ ሁኔታ እየፈጠረ ነው !!

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የአርበኞች ግንቦት 7 ሊቀመንበር

ባለፈው የአርበኞች ግንቦት 7 ጉባኤ ዘገባችን አርበኞች ግንቦት 7 የገጠመውን የመከፋፈልና የመበታተን አደጋ ዋናው መንስኤ ከአርበኞች ግንባር ጋር ያለበቂ ጥናት የተደረገው ውህደት መሆኑን በመጥቀስ የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ድክመቱን በአርበኞች ግንባር የአመራር አባላት ላይ ለማላከክ ጥረት እንዳደረገ መግለፃችን ይታወሳል፡፡

በዚሁ ጉባኤ የተሳተፉት ምንጮቻችን አስመራ በዝግ ከተካሄደው የመጀመሪያው ቀን ስብሰባ ቀጥሎ የነበረውን ሂደት በብዕራቸው የዘገቡልንን እንዳለ እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

በመጀመሪያው ቀን የአስመራ ዝግ ስብሰባ ብርሀኑ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን ካብራራ በኋላ የነበሩትንና ያሉትን እንቅፋቶች ለማስወገድ አዲስ የሚግባባና የሚናበብ አመራር መፍጠር እንደሚያስፈልግ ያለበለዚያ የአርበኞች ግንቦት 7 ውድቀት እውን እንደሚሆን፤ የሚመረጠው አመራርም በኤርትራ ጠቅልሎ መግባት የሚችል መሆን እንዳለበት የጉባዔው ዓላማም ይህ መሆን እንደሚገባው በማሳሰብ ለቀጣዩ ጉባዔ ደጋፊዎቹን ያዘጋጀበትን ስብሰባ በዚሁ መልኩ አጠቃለለ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ከውጭ ሀገር ከመጡት አባላት ጋር የሆቴል ክፍያን በተመለከተ "የትራንስፖርት እራሳችሁ ቻሉ የሆቴሉን ደግሞ እኛ እንችላለ"ን በሚል ከየሃገሩ ሲነሱ ቀደም ሲል ቃል ከተገባው ውጪ አስመራ ከገባን በኋላ የሆቴል ወጫችሁም እራሳችሁ ቻሉ የሚል ያልነበረ አዲስ ሃሳብ በመቅረቡ ለጉባኤ ከተለያየ ሃገር ተጠርቶ የገባው የድርጅቱ አባል ገና ከጅምሩ ከፍተኛ ተቃውሞ አነሳ፡፡ ሁኔታው ያላማረው የድርጅቱ ሊቀመንበር ከሻዕቢያ የቅርብ አለቆቹ ጋር ከተመካከረ በኋላ እሺ መክፈል የምትችሉ ካላችሁ የአልጋ ወጪያችሁን እናንተ ራሳችሁ ብትሸፍኑ፣ የለም አንችልም የምትሉ ከሆነ ግን እኛው እንሸፍነዋለን የሚል ማስታረቂያ የሚመስል ሃሳብ በማቅረቡ ከውጪ የመጣው አባል ተከፋፍሎ በናይል፣ በኒያላና ሌሎች ሆቴሎች እንድናርፍ ተደረገ፡፡ የሚያሳዝነው እነዚህ ሆቴሎች የኮኮብ ደረጃ የተሰጣቸው ቢሆንም በቀን አንድ የውጪ እንግዳ እንኳን የማይጎበኛቸው መሆናቸው ሲታይ ኤርትራ አፍሪካዊትዋ "ሰሜን ኮርያ" የሚል ስያሜ ማግኘትዋ ብዙም የሚገርም አይደለም፡፡

በማግስቱ ጳጉሜ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ተሰብሳቢው በሁለት አውቶቡሶች ተከፍለን እንድንሳፈር ከተደለደልን በኋላ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ራሱ መርጦ ከውጪ ሃገር ያስመጣቸው ደጋፊዎቹን እንኳን ማመን ባለመቻሉ ከሻዕቢያ በተሰጠው ቶዮታ ፒክ አፕ ተሳፍሮ፣ የአርበኞች ግንቦት 7 የበላይ ተጠሪና የዶ/ር ብርሃኑ የቅርብ አለቃ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶችን በተመለከተ የሻዕቢያው ፈላጭ ቆራጭ መኮንን እንደሆነ የሚነገርለት ኮ/ል ፍጹም በሌላ ቶዮታ ፒክ አፕ መኪና ተሳፍረው ጉዞ ጀመርን፡፡

በምዕራባዊ ኤርትራ ጋሽ ባርካ በአንድ ትምህርት ቤት መሰል ግቢ አውቶቡሶቹ ሲደርሱ ቁጥራቸው ከ50 የማይበልጡ እጅግ በጣም የተጎሳቆሉ ያደፈና የነተበ ልብስ የለበሱ የሀዘን ድባብ የሚታይባቸው ወጣቶች ሥርዓት በሌለው መንገድ ተሰልፈው ስናገኛቸው ሁላችንም ደነገጥን፡፡ ከፊታቸው ከወገቡ የጎበጠ እድሜው የገፋ ሽባባው የሚባል የቀድሞ የኢህአፓ አባልና ከአሜሪካ ድርጅቱን የተቀላቀለ ቆሞ የልጆቹን ሰልፍ ሲያስተባበር ተመለከትን፡፡

የወጣቶቹን ሁኔታ የተመለከተው ሁሉም ከውጪ የመጣው ተሰብሳቢ በከፍተኛ ድንጋጤና ሀዘን ውስጥ ገብተን ሁላችንም ማልቀስ ጀመረን፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በዚህ ጉባዔ ላይ ከሠራዊቱ ውስጥ 50 የማይሞሉ አባላት እንደሚሳተፉ እነርሱም በአንጻው የተለያየ በደል (እስር፣ ግርፋት፣ ከባድ የጉልበት ሥራ የደረሰባቸው ናቸው በማለት አስመራ በተካሄደው የመጀመሪያው ቀን ዝግ ስብሰባ የተናገረው ይህንን ጉድ አይተን እንዳንደነግጥ አስቀድሞ ለማዘጋጀት የታቀደ እንደነበር የገባን ይህንን ከጠበቅነው በላይ የሆነው አሳዛኝ ትእይንት በአይናችን በብረቱ ካየን በኋላ ነበር፡፡ እነዚህ ወጣት የኢትዮጵያ ልጆች በድርጅቱ ፕሮፓጋንዳ ተታልለው ኤርትራ ውስጥ እውነት ትግል ያለ መስሎዋቸው ከድርጅቱ ጎን ተሰልፈው ለመታገል ወደ ኤርትራ ከገቡ በኋላ ያለ በቂ የምግብ አቅርቦት በሻዕቢያ እርሻ በነፃ ሲሰሩ ከርመው ለጉባኤው ማድመቂያ ተብሎ ከየማሳው ተሰብስበው የመጡ መሆናቸውን ልጆቹ ራሳቸው በአንደበታቸው ሲናገሩ ሰማን፡፡

ሽባባው ሰልፈኛውን ተጠንቀቅ ሲል ሁሉም ወጣቶች በጦር መሣሪያ ምትክ በእጃቸው በያዙት የተለያየ መጠን ያለው እንጨት ቀና በማድረግ መዝሙር መዘመር ጀመሩ፡፡ መዝሙሩን ከጨረሱ በኋላ ከውጪ ከመጣነው እንግዶች ጋር ሰላምታ የተለዋወጡ ሲሆን በቅርበት የመመልከት እድሉ ስናገኝ ወጣቶቹ ከማሳ ብቻ ሳይሆን ከአንድ ከማይሙች የማጎሪያ ካምፕ ለሰልፍና ለማስመሰል ቲያትር የመጡ መሆኑን ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብንም፡፡

ከልጆቹ ጋር ተቀላቅለን በግል መነጋገርና ማውራት ስንጀምር ኤርትራ ውስጥ የአርበኞች ግንቦት 7 የሚባል ሰራዊት እንደሌለ፤ ብዙዎቹ በሃሬና እና አካባቢው በሻዕቢያ ወታደሮች ጥበቃና ቁጥጥር ታግተው እንደሚገኙ፣ እነሱም የእርሻ ሥራ በመስራት ጊዜያቸውን ያሳልፉ የነበረ ሲሆን አብዛኛዎቹ ወጣቶች የመአዛው ጌጡ አድናቂ መሆናቸውን ሲናገሩ መስማት ቻልን፡፡

ከዚህ አሳዛኝ ትዕይንት በመቀጠል ከውጪ የመጣን የድርጅቱ አባላትና ወጣቶቹ ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንድንገባ ሲደረግ መአዛው ጌጡ በኮሎኔል ፍጹምና ሚካኤል፣ በታጠቁ የሻዕቢያ ወታደሮች ታጅቦ ወደ አዳራሹ ሲገባ ተመለከትን፡፡ ሁኔታው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አስመራ ውስጥ አስቀድሞ እንደነገረንና ቀድሞ እንደተወራው አርበኛው መዓዛው ጌጡ በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር እንደሚገኝ ለማንም ግልፅ ነበር፡፡ ኑርጀባ አሰፋ እና አሰፋ ማሩ /አመነሸዋ/ ከነአምን ዘለቀ ጋር ተከታትለው ወደ ስብሰባው አዳራሽ ገቡ፡፡

ተሰብሳቢው ቦታውን እንደያዘ የደርጅቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የመክፈቻ ንግግር አደረገ፡፡ በወቅቱ መአዛው ጌጡ ምንም ሳይናገር በማግስቱ ስብሰባው እንደሚቀጥል ተገልፆ በሜዳ

የተዘጋጀልንን የምግብና የመጠጥ ግብዣ ተጀመረ፡፡ በግብዣው የመጠጥ ሃይል ዶ/ር ብርሃኑና እነ ኮሎኔል ፍፁም ሰክረው ህሊናቸውን ስተው ሲወላገዱ የተመለከተው የድርጅቱ የዲያስፖራ አባል ያየውን ማመን አቃተው፡፡ የሻዕቢያ ሰዎች መአዛው ጌጡን ከተቀመጠበት በግድ አስነስተው ከብርሃኑ ጋር እንዲጨፍር ሲያደርጉ ለሚድያ ፍጆታ እንዲውል ሆን ተብሎ ታስቦበት የተካሄደ ድራማ እንደነበር የገባን ግን በኋላ ፎቶግራፉ በየሶሻል ሚዲያው ከተሰራጨ በኋላ ነበር፡፡

በጉልበት ስራና በምግብ እጦት የተንቆሳቆሉት ወጣቶቹ ከመጠጡ ትንሽ ከተጎነጩና ከሰከሩ በኋላ ያልጠበቅነው እና ሁላችንም ያሰደነገጠ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ሁሉም በአንድነት መአዛው ጀግና ብርሃኑ ነጋ የሻዕቢያ ሙሽራ እያሉ ያለምንም ፍራቻ መጮህ ሲጀምሩ ሁላችንም ብርክ ያዘን፡፡ የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም ነው ነገሩ፡፡

በማግስቱ የሻዕቢያ ሰዎች አስቀድመው ቦታቸውን እንዲይዙ ከተደረገ በኋላ አስቀድሞ አስመራ ውስጥ በተካሄደው ስብሰባ ከተነገረን ውጪ ለይስሙላ ኑርጀባ አሰፋ የጉባኤው አዘጋጅ ተብሎ በመድረክ ላይ ቢቀመጥም ብርሃኑ ነጋ ከታች ሆኖ አጠቃላይ ሂደቱን በበላይነት ሲመራው ተመለከትን፡፡ በዚህ ሁሉ ትእይንት ውስጥ መአዛው ጌጡ እጁን አፉ ላይ አድርጎ በመገረም ሲመለከት ነበር፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጉባዔው ሲከፈት የመጀመሪያ ቀን ከውጭ ሃገር ለመጣነው አባላት ያደረገውን ንግግር ለተሰብሳቢው ጆሮ በሚመጥን መልኩ በጽሑፍ በሪፖርት መልክ አቀረበ፡፡

ሪፖርቱ በዋናነት ባለፈው ሁለት ዓመት በአመራሩ መካከል በተፈጠረው ውዝግብ ምክንያት ምንም ሥራ ሳይሰራበት የባከነ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ሁላችንም ማመን ያቀተንን ድርጅቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ችግሮች እንዳሉበት ገለፀ፡-

- ለትግል የሚሆን በቂ ገንዘብ አለመገኘቱን ፣
- የአልባሳት አቅርቦት፣ የቀለብ እጥረትና የጥራት ችግር መኖሩን ፣
- በጥይት እጥረት ስልጠና የወሰዱ የተኩስ ልምምድ አለማድረጋቸው፣
- የሠራዊቱ በተለያየ ምክንያት መክዳት (በፍርሃት፣ የመሣሪያ ፍቅር፣ ግዳጅ የለም ኩርፊያ፣ ግዳጅ ሲሰጥ ማፈግፈግ፣ ከትምህርትና ስልጠና መቅረት.....)
- ከኤርትራ የሚደረጉ ድጋፎች በምክትል ሊቀመንበሩ በኩል (መዓዛው ጌጡ መሆኑ ነው) ለሠራዊቱ አለመድረሱ፣
- ድርጅቱ ወደ ሃገር ውስጥ ገንዘብ ማስገባት አስቸጋሪ እንደሆነበት፣
- ድርጅቱ ከአገር ቤት ወያኔ የሚልካቸውን ሰርጎ ገቦች ፈፅሞ መቆጣጠር እንዳልተቻለ፣

- የመገናኛ ሬዲዮ ባለመኖሩ በስልክ የሚደረገው ግንኙነት እየተጠለፈ የድርጅቱ አባላት በወያኔ እየተያዙ መሆኑን፣
- ድርጅቱ የተቀናጀ እና ብቃት ያለው አመራር እንደሌለው ፣
- በአማራነት ዙሪያ በድርጅቱ ላይ እየተነሳ ያለው አሉባልታ እና ወደ ዘር አደረጃጀት ማዘንበል ወዘተ ለአርበኞች ግንቦት 7 ህልውና አደገኛ ሁኔታ እየፈጠረ መሆኑን የሚገልፅ ይዘት ያለው ተስፋ አስቆራጭ ሪፖርት አቀረበ፡፡

ይቀጥላል....